# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ነሐሴ 14 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ የቻይና ጉብኝት እና ልመና እንዳሰበው አልተሳካለትም ተባለ፤**

**የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በሀገሪቱ ርሀብ የለም ሲል በዜጎች ላይ ተሳልቆ መግለጫ መስጠቱ ህዝቡን እና ምሁራኑን አበሳጨ፤**

**በደቡብ ክልል የቢቢሲን ዘገባ ተከትሎ አራት ባለስልጣናት ከስልጣናቸው ተነሱ፤**

ዜጎች በረሀብ እና በችጋር እየተሰቃዩ .......የወገን ያለህ እያሉ የድረሱልን ጥሪ እያሰሙ ....... ነጋዴው የግብር እዳው በዛብኝ እያለ በሚጮህበት.....ከተሜው የኑሮ ውድነቱ ከአቅሙ በላይ ሆኖ የአምላኩን ድጋፍ እየለመነ.....ገበሬው በማዳበሪያ እና በምርጥ ዘር እጦት ተቸግሮ ቀዬውን ጥሎ እግሩ ወዳመራው እየተሰደደ ባለበት በዚህ ግዜ የህዝቡን ችግር ወደጎን ትቶ የውስጥ ችግሩን ለማርገብ ሲል ብቻ ከተያዘለት ፕሮግራም አስቀድሞ ወደ ቻይና ያመራው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ያሰበው እንዳልተሳከለት ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ችግሬን ይቀርፋልኛል.....ምዕራቦች ቢያስከፉኝ በእነሱ እመካለሁ.....እርዳታ ባጣ ብድር ከቻይና አገኛለሁ.....መሸሸጊያም መጠጊያም ይሆኑኛል ያላቸው የቻይና ባለስልጣናት እንዳሰበው ሆነው ያላገኛቸው መሆኑ ከውጤቱ ሊታወቅ ይቻላል የሚል አስተያየት ብዙዎች ይሰጣሉ፡፡

መለስ ወደ ቻይና የተጓዛው ከተያዘለት እቅድ ሶስት ቀናት አስቀድሞ ወደቸ የቢቢሲ ጋዜጠኞች ያጠናቀሩትን ዘገባ ለዓለም ህዝብ ባሰራጩ በሁለተኛው ቀን ሰሆን ፈጥኖ ሊሄድ የተገደደው በሁኔታው በመበሳጨቱ ነው የሚል አስተያየት ብዙዎች ይሰጣሉ፡፡ ይሁን እንጅ እዚያም እንደገባ

የቻይናው ጠቅላይ ሚኒስትር ያነጋገረው ከሶስት ቀን ቆይታ በሁዋላ መሆኑ የበለጥ እንዳበሳጨው ይገመታል።

መለስ ከቻይና ባለስልጣኖች ይልቅ ባለሀብቶችን ሲያነጋግር የሰነበተ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ባለሀብቶቹ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በርካሽ መሬት እንደሚሰጣቸውም ቃል የገባላቸው መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል። ምንም እንኩዋን ከፍተኛ ባለስልጣኖችን ከቀናት ቆይታ በሁዋላ ያነጋገረ ቢሆንም 500 ሚሊዮን ዶላር በብድር 50 ሚሊዮን ዶላር ለድርቅ እርዳታ ከማግኘቱ ሌላ ያሰበውን ያህል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ሳያገኝ ቀርቷል። በተለይ በየአመቱ ከ1.5 ቢሊዮን ብር በላይ ከምእራብ አገሮች በእርዳታ መልክ ብቻ በማግኘት ሲምነሸነሽ የነበረው መለስ የቻይናው የ500 ሚሊዮን የረዢም ጊዜ ብድር ከሚጠብቀው በታች ሆኖበት ሊያበሳጨው እንደሚችል ይገመታል።

ክረምቱን አጫጭር የፖለቲካ ተሀድሶ እንዲሰጣቸውና ያሳለፉትን ዓመት ለመገምገም የወያኔ ካድሬ አምባሳደሮች ከየተመደቡበት ሀገሮች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በታዘዘው መሰረት አብዛኞዎቹ ሳይመጡ የቀሩ ሲሆን ስዩም መስፍንም በዚያው በቻይና መለስ ዜናዊ የሚያደርገውን ጉብኝት እና የማግባባት ስራ እንዲያመቻች የቤት ስራ ተሰጥቶት ስለነበረ ሳይመጣ መቅረቱ ታውቋል።

መለስ ዜናዊ በቻይና ውስጥ የሚያደርገውን ጉብኝት አስመልክቶ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ባለመዘገባቸው የተበሳጩት እነ በረከት ስምኦን የምዕራባውያን ሚዲያዎች የኢትዮጵያን እድገት ሳይሆን ውድቀት የሚመኙ በመሆኑ ይሄንንም ሊያሰራጩ አይፈልጉም እያሉ በሚቆጣጠሩት ራዲዮና ቲሌቪዥን ፕሮፓጋንዳ እየነዙ ከመሆኑም በተጨማሪ ምዕራባውያኖች ይሄን ያደረጉት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በሚሰጡዋቸው ወሬ እየተመሩ ነው በማለትም ተራ አሉባልታ ሲያሰራጩ መክረማቸው ታውቆዋል።

በተያያዘ ዜና በአሁን ሰዓት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰተውንና የዓለምን ህዝብ ጭምር ትኩረት ስቦ ያለውን ርሀብ ሽምጥጦ በመካድ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ርሀብ በሀገሪቱ የለም ሲል ከተጉዋዘበት ቻይና ሆኖ መግለጫ መስጠቱ ምሁራኑን እና ህዝቡን ክፉኛ ማበሳጨቱ ታወቀ።

ሰሞኑን በሰጠው በዚሁ መግለጫ ላይ እንዳለው ከሆነ በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ አንድም የሞተ ዜጋ ባለመኖሩ ርሀብ የለም ያለው መለስ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ለራሳቸው ፕሮፓጋንዳ እንዲያመቻቸው ብቻ ቅመም እየጨመሩ ርሀብ እንደለ አስመስለው ያቀርባሉ እንጂ ፈፅሞ በሀገሪቱ ርሀብ አልተከሰተም ......የለም...... በማለት ድፍረት የተሞላበት መግለጫ መስጠቱ መላ የሀገሪቱን ህዝቦች እንዳሳዘነ ለማወቅ ተችሎዋል።

በአንድ ሀገር ርሀብ አለ ብሎ ለማለት የሚያስችለው ከ10 ሺህ ዜጎች ውስጥ በሰዓት ሁለት ሲሞት ፤የተመጣጠነ ምግብ ሳይኖር ሲቀር፤ቶሎ ለችግሩ ሳይደረስ ሲቀር ነው በማለት ማብራሪያ የሰጠው እብሪተኛው የወያኔ ቡድን መሪ መለስ በአሁኑ ሰዓት ዜጎች እንደቅጠል እየረገፉ...... እየሞቱ..... እየታየ እና የለጋሽ ድርጅቶች ቦታው ድረስ በመገኘት ያረጋገጡትን ሀቅ ሽምጥጦ በመካድ መዋሸቱን ያደመጡ ዜጎች ክፉኛ ሲበሳጩ መደመጣቸው ታውቆዋል።

በሀገሪቱ ርሀብ መኖሩን ደብቆ ስር ሰዶ በመቶዎች የሚቆጠሩ ህፃናት ፤አዛውንት አሮጊቶች እንዲያልቁ ያደረገው ሳያንሰው ዛሬም ረሀብተኞች እርዳታ እንዳያገኙ እያከላከለ መገኘቱ የሚያሰዝን እና የሚያሳፍር ነው ሲሉ ምሁራኖች ጭምር በንዴት እየተናገሩ ይገኛሉ።

ሩቅ ሳንሄድ እዚሁ ከመዲናችን 170 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ አሩሲ ነገሌ በምትባል ወረዳ ውስጥ ዜጎች በአረንጉዋዴ ርሀብ መሞታቸውን የወረዳው ካድሬዎች አረጋግጠው የድረሱልን ጥሪ ሲያሰሙ እንዳልነበር የነበረውን እውነታ ክዶና ዋሽቶ መለስ በቻይና የሄደበት ልመና አልሳካ ሲለው ርሀብተኛ በሀገሪቱ የለም ብሎ መናገሩ አስገራሚና የሰውዬውን የጤንነት ሁኔታ ጥያቄ ላይ የሚጥል ነው ሲሉም የለጋሽ ድርጅት ሰራተኞች ሲገልፁ ተደምጠዋል።

ከአንድ ወር በፊት በደቡብ ኢትዮጵያ በቦረና እና በምስራቅ ኢትዮጵያ በሱማሌ ክልል ውስጥ ከ30 ሰዎች በላይ እንደሞቱና ከ800 ሺህ በላይ ግመሎች እና የቀንድ ከብቶች በርሀቡ ማለቃቸውን የዓለም መገናኛ ብዙሀን ጭምር በምስል አስደገፎ ያሰራጨውን ሀቅ ሽምጥጦ የካደው መለስ አሁንም በችግር ውስጥ ያሉ ዜጎች እርዳታ እንዳያገኙ ርሀብ የለም እያለ እያከላከለ መገኘቱ ሰውዬው ጤንነቱ እጅግ አጠራጣሪ ነው ሲሉ ምሁራኖቹም እንደ ለጋሽ ድርጅት ሰራተኞቹ ይገልፃሉ።

ከአራት ኪሎ ቤተመንግስት በስተቀር በመላ ሀገሪቱ ከፍተኛ ስር የሰደደ ርሀብ መኖሩን የጠቆሙት እነዚሁ ምሁራኖች ሌላው ቢቀር ሩቅ ሳንሄድ በዚሁ በመዲናችን አዲስ አበባ ውስጥ ከሩኛ በርሀብ የተጠቁ ዜጎች ቁጥር የትየለሌ መሆኑ እየታወቀ ያለውን ሀቅ ሽምጥጦ ርሀብ የለም ማለት ፌዝ ነው ሲሉ የመለስን መግለጫ አጣጥለውታል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተወካዮች ባደረጉት አራተኛ ጉባኤ በምስራቅ አፍሪካ የአየር ለውጥ የተከሰተ መሆኑን ጠቅሰው በተለይ በኢትዮጵያ ከቦረና በተሰበሰበ መረጃ መሰረት በየስድስት እና ስምንት ዓመታቶች ውስጥ ከፍተኛ ርሀብ እንደሚከሰት ቅድመ ትንበያ አድርገው እንደነበር ታውቆዋል።

በዚሁ ቅድመ ትንበያ መሰረት አሁን በሀገሪቱ ለተከሰተው ርሀብ የዝናብ እጥረቱ እንደ ምክንያት ቢጠቀስም ዋነኛው ተጠያቂ ግን የሀገሪቱ መሪዎች መሆናቸውን የገለፀው የድርጅቱ ጥናት በተለይ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ያለመስፈን ችግር አንዱና ዋነኛ ምክንያት መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ መግለፁ ታውቆዋል።

አሁን ባለው ተጨባጭ መረጃ መሰረት በ60 ዓመታት ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ኢትዮጵያን ጨምሮ በምስራቅ አፍሪካ የከፋ ድርቅ ተከስቶ ከ12.4 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ለርሀብ ተጋልጦ እያለ እና መረጃዎች በተጨባጭ እያመለከቱ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ግን ርሀቡ አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ድረስ ዘልቆ ባለመግባቱ ብቻ ርሀብ የለም ብሎ መናገሩ በእጅጉ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ከአንድ ጤነኛ አእምሮ ካለው ግለሰብ የሚጠበቅ አይደለም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፈው ሳምንት በኢትዮጵያ ዙሪያ ቢቢሲ ያሰራጨውን ዘገባ ተከትሎ በወያኔ ካድሬዎች መሀከል ከፍተኛ ትርምስ ተፈጥሮ አራት ባለስልጣናት ከስራ ገበታቸው ላይ መባረራቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገለጠ።

በደቡብ ክልል ውስጥ በተፈጠረ ትርምስ የተነሳ ከክልሉ ፕሬዝዳንት ሽፈራው ሽጉጤ ጀምሮ እስከ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሊቀመንበር ድረስ ባሉ የወያኔ ካድሬዎች መሀከል ከፍተኛ ውዝግብ ተፈጥሮ ለአራት ባለስልጣናት ከስራ መባረር እና ለሌሎች አራት ባለስልጣናት ማስጠንቀቂያ መሰጠት ምክንያት እንደሆነ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

ከመለስ ዜናዊ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ሽፈራው ሽጉጤ የዞን ፤የወረዳና የቀበሌ ሹማምንቶችን በግምገማ መልክ ቢያወያይም ሁሉም እርስ በርስ እየተነታረኩ መፍትሄ ባለመገኘቱ አራት ባለስልጣናቱን ከስራ ሙሉ ለሙሉ ሲያባርራቸው አራቱን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ለቢቢሲ ጋዜጠኞች ምስጢር አሳልፋችሁ ሰጥታችሁዋል የተባሉትን በአጭር ቀን ውስጥ መርጠው እንዲያስረክቡት ማስጠንቀቁንም ጨምሮ የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።

ከተባረሩት ባለስልጣናት መሀከል አንድ የዞን አስተዳዳሪ፤አንድ የወረዳ አስተዳዳሪና ሁለት የቀበሌ ሊቀመንበሮች ሲሆኑ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ባለስልጣናት አራቱ ደግሞ የክልሉ የፀጥታና የፍትህ ቢሮ ኃላፊ እና የዞኑ አመራሮች እንደሆኑ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

ከስልጣናቸው ተነሱ የተባሉትን ካድሬዎች ሽፈራው ሽጉጤ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ቃል አቀባይ በማለት ሲወርፋቸው እና ሲዘልፋቸው እንደነበረ ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ በአርሶ አደሮቹ ውስጥ ተሰግስገው ያሉትን የተቃዋሚ ኃይሎችም መመንጠር ግድ ይላል ሲል መናገሩንም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።

የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት የሆነው ይሄው ሽፈራው ሽጉጤ የተሰኘው ሳይጠሩት አቤት...... ሳይልኩት ወዴት..... የሚለው ግለሰብ ከዚህ ቀደም የመለስን ትዕዛዝ ሳይፈጽም በመቅረቱ ለሁለት ወራት ከስልጣኑ ተንሳፍፎ የቁም እስረኛ ሆኖ እንደነበር ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ አሁንም  በዜጎች ላይ የሚፈጸመውን አድልኦ ለቢቢሲ ማስረጃ አሳልፈው የሰጡትን ዜጎች ለቅሞ እንዲያወጣ ከመለስ ጥብቅ ትዕዛዝ ስለተሰጠው በዞንና በወረዳ ብሎም በቀበሌ አመራሮች ላይ ከፍተኛ ጫና ሊፈጥር እንደቻለም ዘገባው አብራርቶዋል።

በመጨረሻም እብሪት እና ትዕቢት የወጠረው የወያኔ ተላላኪ እና የከተማ ታጋይ የሆነው የኦህዴዱ ከፍተኛ ባለስልጣን  ጁኔዲ ሳዶ ባልተገራ አንደበቱ ምሁራኑን ከፍ ዝቅ አድርጎ መሳደቡን የደረሰን ጥቆማ ገለፀ።

እንደ በቀቀን የመለስ ዜናዊን ቃል ብቻ እየደጋገመ የሚተነፍሰው ይሄው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር ጁኔዲ ሳዶ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምሁራኖችን እጅግ በሚያሳዝን እና በሚያሳፍር ሁኔታ እውቀታችሁ የወረቀት ሽምደዳ ብቻ ነው ሲል መሳደቡን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

የፕሮፌሰርነት እና ዶክትሬት ዲግሪ ለማግኘት ብቻ በወረቀት ላይ ሸምድዳችሁ የምትይዙት እንጂ ጠለቅ ያለ እውቀት የላችሁም ያለው ይሄው ግለሰብ ለተማሪዎች እንቅስቃሴና ለውጥ ለማምጣት

የማትጥሩ ደካሞች ናችሁ ሲል አጉራ ዘለል በሆነ አንደበቱ ምሁራኖቹን መዝለፉን ተከትሎ ውዝግብ ተፈጥሮ እንደነበርም ጥቆማው ገልፆዋል።

ለሀያ ዓመታት በመሳሪያና በጦር ኃይል የህዝቡን አንደበት ሸብባችሁ እንዳይናገር እና እንዳይተነፍስ አድርጋችሁ ከማፈናችሁ አልፎ ምሁራኑ በእውቀቱ ሀገሩንና ህዝቡን እንዳያገለግል ዘረኛና መርዘኛ የሆነ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲያችሁን አስርጻችሁ ህዝቡን ለድህነት ሀገሪቱን ለምድረበዳነት እየዳረጋችሁ መልሳችሁ በእኛ ላይ ጣት ለመቀሰር መሮጣችሁ የሚያሰዝን እና የሚያሳፍር ነው ሲሉ ምላሽ እንደሰጡትና በዚሁ ምክንያት በጁኔዲና በተሰብሳቢ ምሁራኖች መሀከል ትርምስ ተፈጥሮ እንደነበር ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

እንደ አለቃው ሁሉ እሱም በቀጠነ እና በሰለለ እጁ ጠረጴዛ እየደበደበ ስህተታችሁን አሜን ብላችሁ ላለመቀበል የምታደርጉት መፍጨርጨር እንጂ አሁንም እወቀታችሁ ለመመረቅና ውጤት ለማመጣት እንጂ ሀገር ለመገንባት አይደለም በማለት በድጋሚ የተናገረው ይሄው ግለሰብ የጀመረውን ሀሳብ ሳይጨርስ ከግማሽ በላይ የሆኑት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራኖች የስብሰባ አዳራሹን ጥለው እንደወጡና ጥቂቶች ብቻ እንደቀሩ ለማወቅ ተችሎዋል።

በምሁራኖቹ እርምጃ የተበሳጨው ይሄው የወያኔ አጨብጫቢ ባለስልጣን በንዴት

በቅርብ ቀን ሁሉም በሚሰማራበት የስራ መስክ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት የሚችልበትንና የሚመዘንበትን መስፈርት አዘጋጅተን ተግባራዊ ስናደርግ እየተራገፋችሁ ትቀራላችሁ በማለት ሲያስፈራራ እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።